ደጀጉ ሬታና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት

# ዘናሆም ነቢይ

## መቅድም

### ጉባዔ

ናሆም: ማለት: ፈውስ: እግዚአብሔር፤ ፈውስ: እግዚአብሔር: ማለት: ነው፤ ትውልዱ፤ ነገዱ: ከነገደ: ዛብሎን: ነው፤ እናቱ: ሶስና: ትባላለች፤ መነሣቱ: በሕዝቅያስ: ዘመን: ነው፤

### ምዕራፍ ፩

፩፤ ተረፈ: ነነዌ: መጽሐፈ: ራእዩ: ለናሆም: ወልደ: ኬልቅዩስ፤

መጽሐፈ: ራእዩ: ለናሆም: ተረፈ: ነነዌ: ሲል: ነው፤ ዮናስ: በነነዌ: ከመናገር: የቀረው: ናሆም: የተናገረው: ነገር: ይህ: ነው፤ አንድም: የኬልቅዩስ: ልጅ: ናሆም: የተናገረው: ብዙ: ነገሩ: ይህ: ነው፤ ይህ: አርእስት: ነው፤ ሠለስቱ: ምዕት: ለመጻሕፍት: አርእስት: ሲሰጡ: አርእስት: ሰጥተውታል፤ እርሱ: ግን: ነገሩን: እግዚአብሔር: ቀናዒ: ብሎ: ያመጣዋል፤

፪፤ እግዚአብሔር: ቀናዒ: ወመስተበቀል፤

እግዚአብሔር: ለአምላክነቱ: ቀንቶ: በዔዋዌ: እስራኤልን፤ በሚጠት: አሕዛብን: የሚያጠፋ: ነው፤

ወይትቤቀሎሙ: እግዚአብሔር: በመዓቱ: ለፀሩ፤

እግዚአብሔር: ጠላቶቹን: ተበቅሎ: ያጠፋቸዋል፤

ወያጠፍኦሙ: ለጸላዕቱ፤

ጠላቶቹን: ያጠፋቸዋል፤ ፀር: ያለው: የዕለት: ጠላት: ነው፤ ጸላዕት: ያለው: ጥንተ: ጠላት: ነው፤

፫፤ እግዚአብሔር: መስተዓግሥ: ወዓቢይ: ኃይሉ፤

እግዚአብሔር: ዕጉሥ: ነው፤ ኃይሉም: ጽኑ: ነው፤

ወንጹሕኒ: አልቦ: ንጹሕ: በኀቤሁ፤

በሱ: ዘንድ: ንጹሕ: የለም፤ አንድም: ንጹሕ: ነኝ: የሚል: ሰው: ሁሉ: በሱ: ዘንድ: ንጹሕ: አይደለም፤ ሰማይኒ: ኢኮነ: ንጹሐ: እንዲል፤

እግዚአብሔር: በፍጽም: ወበድኅር: ፍኖቱ፤

እግዚአብሔር: ከፊት: በር: እስከኋላ: ዳረገንድ: የሰፈሩትን: ያጠፋል፤ አንድም: በፊት: የደረሰውን: በፊት፤ በኋላ: የደረሰውን: በኋላ: ያጠፋል፤ አንድም: ብልጣሶርን፤ ሰናክሬምን: ያጠፋል፤

ወይከውኑ: ከመ: ፀበል፤

እንደ: ትቢያ: ይሆናሉ፤ ወደመና: ጸበለ: እገሪሁ: የሚል: ይገኛል: ሳታናብብ፤ አንድም: በዓውሎ: ወበድልቅልቅ: ፍኖቱ: ይላል፤

ወይሬስዮሙ: ከመ: ደመና፤

ደመና: ተበትኖ: እንዲጠፋ: ያጠፋቸዋል፤

፬፤ ወያጠፍዓ: ለባሕር ወያየብሳ፤

ነነዌን: ፈጽሞ: ያጠፋታል፤

ወያነጽፎሙ: ለኵሎሙ: አፍላግ:

ፈሳሾች: ውሆችን: ያጠፋቸዋል: ማለት: ነገሥታቱን: ከተድላ: ከደስታ: ይለያቸዋል፤

ኃልቁ: ባሳን: ወቀርሜሎስ፤

ባለጸጎች: ሁሉ: ይጠፋሉ፤

ወጠፍአ: ኵሉ: ፍሬ: ሊባኖስ፤

ባለጸግነታቸው: ሁሉ: ይጠፋል፤

፭፤ ወአድለቅለቁ: አድባር: እምኔሁ፤

ከሱ: የተነሣ: ተራሮች: ተነዋወጡ፤

ወአንቀልቀሉ: አውግር፤

ኰረብታዎች: ተነዋወጡ: ማለት: በዔዋዌ: የጽኤል: ነገሥታቱ:



መኳንንቱ፤ በሚጠት: የአሕዛብ: ነገሥታቱ፤ መኳንንቱ: ጠፉ፤

ወደንገፀት: ምድር: እምቅድመ: ገጹ፤

ከገጹ: መዓቱ: የተነሣ: የሰናክሬም፤ የብልጣሶር: ከተማ: ተነዋወጠች፤

ወኵሎሙ: እለ: ይነብሩ: ውስቴታ፤

በርሷ: የሚኖሩ: ሰዎች: ሁሉ: ይደነግጣሉ፤

፮፤ ወመኑ: ይትቃወማ: ለመቅሠፍተ: መዓቱ፤

ተቆጥቶ: ያመጣትን: መቅሠፍት: ማን: ይቃወማታል፤

ወመዓቱሂ: ይመስዎሙ: ለአድባር: አርእስቲሆሙ፤

መዓቱም: የነገሥታቱን: ሥልጣን: ያጠፋል፤

ወይትቀጠቀጥ: ኰኵሕ: እምኔሁ፤

ከመዓቱ: የተነሣ: ደንጊያው: ይሰበራል: ማለት: ዓርበኛው: ይጠፋል፤

፯፤ ኄር: እግዚአብሔር: ለእለ: ይትዔገሥዎ: በዕለተ: ምንዳቤሆሙ፤

ለፈተና: ብሎ: መከራ: ቢያመጣባቸው: መከራውን: ታግሠው: ለሚቀበሉ: ሰዎች: እግዚአብሔር: ቸር: ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወየአምሮሙ፡ ለእለ፡ ይፈርህዎ፤

የሚያመልኩትን፤ የሚፈሩትን፡ ሰዎች፡ እግዚአብሔር፡ ይወዳቸዋል።

፰፤ ወይሬእዮሙ፡ ለእለ፡ ይትነሥኡ፡ በእኩይ፤

በክፉ፡ ነገር፡ የሚነሡትን፤

ከመ፡ ይሕልቁ፡ በፍኖተ፡ አይኅ፤

ማየ፡ አይኅን፡ በመሰለ፡ መቅሠፍት፡ እንዲጠፉ ያደርጋቸዋል።

ወይዴግኖሙ፡ ጽልመት፡ ለፀሩ፤

ጠላቶቹን፡ ጽኑ፡ መከራ፡ ያገኛቸዋል።

፱፤ ምንተ፡ ይሔልዩ፡ ላዕለ፡ እግዚአብሔር፤

እንዲህ፡ ባደረገ፡ ጊዜ፡ በእግዚአብሔር፡ ላይ፡ ምን፡ ያስባሉ።

ናሁ፡ ውእቱ፡ ይገብር፡ ማኅለቅተ፤

እነሆ፡ እሱ፡ ፍጻሜ፡ ጥፋትን፡ ያደርጋል።

ወይትቤቀል፡ እንከ፡ ካዕበ፡ ኅቡረ፤

በሕማም፤ በመከራ፡ ተይዘው፡ ሳለ፡ እንግዲህ፡ ወዲህ፡ በአንድነት፡ ያጠፋቸዋል።

፲፤ እስመ፡ መሠረቶሙ፡ ትማስን፡

ከተማቸው፡ ትጠፋለችና፤ አንድም፡ የትሑታኑ፡ መሠረት፡ የማሆኑ፡ ነገሥታቱ፡ ይጠፋሉና፤

ወትትበላዕ፡ ከመ፡ ብላዕ፡ ዕፂ፤

አሥሩ፡ ነገድ፡ ነቀዝ፡ እንደበላው፡ እንጨት፡ ይጠፋሉ።

ወትትበላዕ፡ ከመ፡ ብርዕ፡ ባሕሩስ፡ ይቡስ፤

ሁለቱ፡ ነገድም፡ እንደ፡ ደረቀ፡ መቃ፡ መስዬ፡ ገለባ፡ ይጠፋሉ።

፲፩፤ እስመ፡ እምኔከ፡ ይወጽእ፡ ሕሊና፡ እኩይ፡ ላዕለ፡ እግዚአብሔር፤

ሰናክሬምን፡ እንዲህ፡ ይለዋል፤ ቦኑ፡ ግልፎ፡ ዘያድኅን፡ እያልህ፡ በእግዚአብሔር፡ ክፉ፡ ነገር፡ ትናገራለህና፤ አንድም፡ ብልጣሶርን፡ እንዲህ፡ ይለዋል፤ በጸሕሉ፡ ፊትፍታችሁ፡ አበሉበት፤ በፅዋው፡ ቀድታችሁ፡ አጠጡበት፡ ብለሃልና፤ አንድም፡ ብልጣሶር፡ የእስራኤል፡ ፈጣሪ፡ ምን፡ ቁም፡ ነገር፡ ነው? አያድን፡ አይረዳ፡ ትላለህና፤ አንድም፡ ሰናክሬም፡ ቦኑ፡ ግልፎ፡ ትላለህና፤ አንድም፡ ዲዮብሎስ፡ አነ፡ ፈጣሪሆሙ፡ ትላለህና፤

ወትመክር፡ ኅሡመ፤

ክፉ፡ ነገር፡ ትመክራለህ፤ ትርጓሜው፡ እንዳለፈው፡ ነው።

፲፪፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ እንተ፡ ማይ፡ ብዙኅ፡ ዘይውኅዝ፡ ወይነጽፍ፡ ከማሁ፡ ነገርከ፡ ኢይሰማዕ፡ እንከ፤

በገዞ፡ የሚፈስ፡ የኅርፍ፡ ውሀ፡ ፈጥኖ፡ [illegible]



ሰናክሬም፡ ብልጣሶር፡ እንደዚህም፡ ሁሉ፡ ነገርህ፡ አይሰማም።

፲፫፤ ወናሁ፡ ይእዜ፡ እቀጠቅጣ፡ ለበትሩ፡ እምኔከ፤

ሕዝቅያስ፡ የሰናክሬምን፡ አምዝዝ፡ ከአንተ፡ አርቅልሃለሁ።

ወእበትክ፡ ማሐሚከ፤

አምዝዝህን፡ አጠፋለሁ።

፲፬፤ ወይኤዝዝ፡ እግዚአብሔር፡ በእንቲአከ፡ ከመ፡ ኢይሰማዕ፡ ስምከ፤

እግዚአብሔር፡ ስምህ፡ እንዳይጠራ፡ በአንተ፡ መዓት፡ መቅሠፍት፡ ያዝዛልና።

ወዓዲ፡ እሰርዎ፡ ለግልፎከ፡ እምቤተ፡ አምላክከ፤

ዳግመኛ፡ የተቀረጸ፡ ጣዖትህን፡ ከጣዖት፡ ቤት፡ አጠፋለሁ።

ወፍጡነ፡ እሬስዮ፡ መቃብረከ፡ ለስብከከ፤

ጣዖትህን፡ ፈጥኜ፡ መቃብርህ፡ አደርገዋለሁ፤ የሰናክሬም፡ ያሉ፡ እንደሆነ፡ የተመቸ፡ ነው፤ የብልጣሶር፡ ያሉ፡ እንደሆነ፡ ምክንያተ፡ ሞት፡ አደርገዋለሁ፡ ሲል፡ ነው።

፲፭፤ ናሁ፡ ውስተ፡ አድባር፡ እገሪሆሙ፡ ለሰብአ፡ ዜና፤

ወሬ፡ የሚያወሩ፡ ሰዎች፡ እግራቸው፡ በተራራ፡ ላይ፡ ቆሟል።

ወይዜንዉ፡ ሰላመ፤

[illegible]

ግበር፡ በዓለከ፡ ይሁዳ፤

እንዲህ፡ ነውና፡ ይሁዳ፡ በዓለ፡ ሠዊትን፡ በዓለ፡ መጸለትን፡ አክብር፤

ወፍዲ፡ ብፅዓቲከ፤

ከባቢሎን፡ ብቻ፡ ብታወጣኝ፤ ኢየሩሳሌም፡ ብታገባኝ፡ ይኸን፡ እሰጣለሁ፡ ብለህ፡ የተሳልከውን፡ ስዕለትህን፡ ስጥ።

እስመ፡ ኢይደግሙ፡ እንከ፡ ወኢይመጽኡ፡ ይትጋደሉከ፤

ይዋጉህ፡ ዘንድ፡ ዳግመኛ፡ ወደ፡ አንተ፡ አይመጡምና።

ኃልቀ ወተሥዕረ፤

የሰባው፡ ዘመን፡ መከራ፡ ተፈጸመ፤ አንድም፡ ናሁ፡ እገሪሆሙ፡ ውስተ፡ አድባር፡ ብለህ፡ መልስ፤ ስብከተ፡ ሐዋርያት፡ በትንቢተ፡ ነቢያት፡ ጸንቷል፤ ወይዜንዉ፡ ሰላመ፤ ወንጌልን፡ ያስተምራሉ፤ እንዲህ፡ ነውና፤ ይሁዳ፡ ዘነፍስ፡ በዓለ ትንሣኤን፡ አክብር፤ ከሲኦል፡ ብታወጣኝ፡ ለልጅነት፡ ብታበቃኝ፡ ይኸን እሰጣለሁ፡ ብለህ፡ የተሣልከውን፡ ስዕለት፡ ስጥ፤ ይዋጉህ፡ ዘንድ፡ አጋንንት፡ ወደ፡ አንተ፡ አይመጡምና፡ ያምስቱ፡ ሺህ፡ ካምስት፡ መቶ፡ ዘመን፡ መከራ፡ ተፈጸመ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፪

፩፤ ወአልቦ: ዘይነፍሕ: ቅድመ: ገጽከ፣

ጥቂት: መከራ: የሚያመጣ ብህ: የለም፤

ወያጠፍአከ: በሕማም፣

በመከራም: የሚያጠፋህ: የለም፤

አስተሐይጽ: ፍኖተከ፤

ዘሩባቤል: ሚጡትን: ተመልከት፤

ወአጽንዕ: ሐቌከ፣

ወገብ: ልቡናህን: አጽና፤

አጥብዕ: በኃይልከ: በሕቁ፣

ፊጽመህ: ጨክን፤

፪፤ እስመ: ሜጠ: እግዚአብሔር: ጽዕለተ: ያዕቆብ: ወፅዕለተ: እስራኤል፣

ያሥሩን: ነገድ: የሁለቱን: ነገድ: ስድብ: ወደ: አሕዛብ: መልሷልና፣ ዐሥሩ: ነገድ፣ ሁለቱ: ነገድ: የሚሰድቡትን: ስድብ: መልሷልና፣ አስተሐይጽ: ላለው፣

እስመ: ነጺሐ: ነጽሕዎሙ፣

በጦር: እየወጉ: ስለጣሏቸው፤

ወአማሰኑ: አዕፁቂሆሙ፣

ልጆቻቸውን: አጠፉ፤

፫፤ በወልታ: ኃይሎሙ: እምሰብእ: ዕደው: ኃያላን: እለ: ይረውፁ: ከመ: እሳት፣

እንደ: እሳት: ፈጥነው: ከሚደርሱ: ከኃያላኑ: ሰይተው: ኃይላቸውን: በሚገልጡበት: በጋሻቸው: በጦራቸው: ልጆቻቸውን: ስለአጠፉ፤

ሶበ: ይትሬስዩ: ውስተ: ሠረገላቲሆሙ፣

በሠረገላቸው: በተቀመጡ: ጊዜ፤

ወአፍራሲሆሙኒ: ይትሀወኩ: ውስተ: ፍኖት፣

የአሕዛብ: ፈረሶቻቸው: በጎዳና: ያዙን: ልቀቁን: ይላሉ፣

፬፤ ወይደነግፁ: ውስተ: ሠረገላት፣

በሠረገላ: የተቀመጡ: ሰዎች: ይደነግጣሉ፤ አንድም: በፈረስ: የተቀመጡትን: ሰዎች: ባዩ: ጊዜ: በሠረገላ: ያሉት: ሰዎች: ይደነግጣሉ፤

ወይትጓድዐ: በፍኖት፣

በጐዳና: ጋሻ: ለጋሻ: ይጣፋሉ፤

ገጾሙ: ከመ: ነበልባለ: እሳት፣

ፊታቸው: የቋያ: እሳት: ነው፤

፭፤ ወከመ: መብረቅ: ዘይረውፅ: ይረውፁ: መሳፍንቲሆሙ፣

ሹማምንቱም: ፈጥኖ: እንደሚሰማ: መብረቅ: ናቸው፤

ወይሜምዑ:መዓልተ፣

በመዓልት: ይሸበራሉ፤

ወይደክሙ: በፍኖት፣

በጐዳና: ይደክማሉ፤

ወይረውፁ: ዲበ: አረፋቲሃ፣

ቅጽሩዋን

www.ethiopianorthodox.org



ወያነብሩ: መዓቅቢሆሙ፣

የሚወጣውን:የሚገባውን:ያይ: ዘንድ: ዘበኛ: ያኖራሉ፤

፮፤ ወይትረኃዎ: አናቅጸ: አህጉር፣

የሀገሩ: ሁሉ: በሮች: ይከፈታሉ፤ አንድም: አርበኞች: ይጠፋሉ፤

ወይወድቁ: አብያተ: መንግሥት፣

የነገሥታቱ: ወገኖች: ይጠፋሉ፤ አንድም: የነገሥታቱ: ቤቶች: ተፈቱ፤

፯፤ ወተከሥተ: ኃይል፣

በማጀት: የተቀበረው: ባለጸግነታቸው: ተገለጠ፤

### ጉባዔ

ወዐርገት: ይእቲ: ባቢሎን፣

ባቢሎን: ወደምትጠፋበት: ቦታ: ወጣች፤ አንድም: እንዲህ: እንዲህ: ታደርግ: የነበረች: ባቢሎን: ለጥፋት: ቀረበች፤ አንድም: ቀርባለችና፣ አስተሐይጽ: ላለው፤

ወአዕማቲሃ: ይመርሐ፣

ቂሮስ: ዳርዮስ: ወደምትጠፋበት: ቦታ: ይመሩዋታል፤ አንድም: ጥቃቅኑ: አህጉር፤ አንድም: ትገዛቸው: የነበሩ: እስራኤል: ወደምትጠፋበት: ቦታ: ይመሯታል፤

ወከመ: ርግብ: ይነቅዋ: በልቦን፣

ፊርተው: እንደርግብ: በልቡና

፰፤ ወነነዌስ: ከመ: ምጥማቃተ: ማይ: ብዕላ፣

ብዕላ: ለነነዌ: ሲል: ነው፤ እንደ: ውሀ: ብዙ: የሆነ: የነነዌ: ብዕሏ: ይጠፋል፤

እሙንቱስ: ጐዩ: ወኢቆሙ፣

ነገሥታቱ: ሸሹ፣ ጸንተው: አልተዋጉም፤

ወአልቦ: ዘይትመየጥ፣

አግባ: መልስ: ብሎ: የሚዋጋ: የለም፤

፱፤ በርበሩ: ኅብሩረ: ወወርቀ፣

ወርቁን: ብሩን: በዘበዙ፤

ወአልቦ: ማኅለቅት: ለሠርጓ፣

ለሽልማቷ: ፍጻሜ: የለውም፤

፲፤ ወክቡድ: ኵሉ: ንዋያ: መፍትው: ተነግፈ: ወተገድፈ፣

ገንዘቧ: ብዙ: ነበረ፣ ስንኳን: በሚገባ: ጠፋ፤

ወተሐቅየ: ስነን: ወደንገፀ: ልብ፣

ጥርስ: ተፋጨ: ልቡናም: ደነገጠ፤

ወርእደ: ብርክ: ወተቀጽአ: ኵሉ: ሐቌ፣

ጉልበትም: ብርክርክ: አለ፣ ወገብም: ጐበጠ፤

ወይከውን: ገጸ: ኵሉ: ከመ: ጸለሎ: መቅጹት፣

የሰው: ሁሉ: ፊት: እንደ: ድስት: ጥላት: በመከራ: ይጠቁራል፤

አንድም፡ ከመ፡ ዘጸለሎ፡ መቅ ጹት፡ ይላል፤ በድስት፡ ውስጥ፡ እንደሚቀቀለው፡ ሥጋ፡ ይሆ ናል፤ ያ፡ እንደሚለያይ፡ ሰውነቱ፡ እለይ፡ እለይ፡ ይላል፤

፲፩፤ አይቴ፡ ውእቱ፡ ማኅበሊሆሙ፡ ለአናብስት፤

የነገሥታቱ፡ ከተማ፡ ወዴት፡ነው፤

ወአይቴ፡ ይትርአዩ፡ ዕጓለ፡ አናብስት፤

የነገሥታቱ፡ ልጆች፡ ወዴት፡ ደረሱ፤

አይቴ፡ ሖረ፡ ዕጓለ፡ አንበሳ፡ ከመ፡ ይባዕ፡ ህየ፡ ዕጓለ፡ አንበሳ፤

ቂሮስ፡ ወደ፡ ከተማ፡ ይገባ፡ ዘንድ፡ ብልጣሶር፡ ወዴት፡ ደረሰ፤

ወአልቦ፡ ዘይጌርሞ፤

የሚያስፈራው፡ የለም፤

፲፪፤ አንበሳ፡ መሰጠ፡ ዘየአክሎሙ፡ ለዕጐሊሁ፤

ቂሮስ፡ ለልጆቹ፡ የሚበቃውን፡ ያህል፡ ሰበሰበ፤ አንድም፡ ለሠ ራዊቱ፤

ወመልዓ፡ ወርቀ፡ ለአንስቲያሁ፡ ወአ ነቀ፡ በእንቲአሁ፤

እሱን፡ ድል፡ ስለነሣ፡ ለነሱ፡ ዝርግፍ፡ ወርቅ፡ አሠራላቸው፤ ለሚስቶቹ፡ አብዝቶ፡ ሰበሰበ፤

ወመልዓ፡ እምነ፡ ዘነዓወ፡ ለዕጐሊሁ፡ ግቦ፡ እምዘ፡ መሠጠ፤

እምዘ፡ ነዓወና፡ እምዘ፡ መሠጠ፡ አንድ፡ ወገን፤ ማርኮ፡ ካመጣው፡ ከገንዘቡ፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ ለል ጆቹ፡ ሲሆን፡ በከተማው፡ መላ፤

፲፫፤ ናሁ፡ አነ፡ ላዕሌከ፡ ይቤ፡ እግ ዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ ሰናክሬም፡ እነሆ፡ በመዓት፡ በአንተ፡ ላይ፡ አለሁ፡ አለ፤

ወአነድዶሙ፡ በእሳት፡ ለብዝኀከ፤

ሠራዊቶችህን፡ በሰይፈ፡ መል አክ፡ አጠፋቸዋለሁ፤

ወትበልዖሙ፡ ኵናት፡ ለአናብስቲከ፤

አርበኞችህን፡ ጦር፡ ታጠፋ ቸዋለች፤

ወአጠፍዓ፡ ለምድር፡ እማዕገትከ፤

ከባቢ፡ ጦርህን ከዚህ፡ ዓለም፡ አጠፋታለሁ፤

ወኢይሰማዕ፡ እንከ፡ ምግባሪከ፤

በዚህ፡ ጊዜ፡ ዘመተ፤ በዚህ፡ ጊዜ፡ ተመለሰ፡ የሚልህ፡ የለም።

## ምዕራፍ ፫

፩፤ አሌላ፡ ለሀገረ፡ ደም፤

የሰውን፡ ደም፡ ለምታፈስ፡ ለነ ነዌ፡ ወዮላት፤

እንተ፡ መልዓት፡ ሐሰተ፡ ወዘገብረት፡ ዓመፃ፤

ጣዖትን፡ ቅሚያን፡ ላበዛች፡ ለነ ነዌ፡ ወዮላት፤

ወኢይትገሐሥ፡ ማዕገተ፡ መቅሠፍታ፤

ከባቢ፡ ጦር፡ አይርቅላትም፤

፪፤ መዓት፡ ወቃለ፡ መንኰራኵር፡ ወድልቅልቅ፤

የእግዚአብሔር፡ መዓት፡ የሠ ረገላ፡ ድምፅ፡ ንውጽውጽታ፡ ከሷ፡ አይ[illegible]



ወድምፀ፡ አፍራስ፡ ዘይረውፅ፡ ወሠ ረገላ፡ ዘይረውፅ፤

ፈጣኖች፡ የሆኑ፡ የሠረገላዎ ችና፡ የፈረሶች፡ ድምፅ፡ ከሷ፡ አይርቅም፡

ወመስተፅዕናን፡ ዘይጊዓኑ፤

በፈረስ፡ የተቀመጡ፡ ሰዎች፡ ከሷ፡ አይርቁም፤

፫፤ ወኲናተ፡ ይመልሱ፡ ላዕሌሃ፡

የጦሩን፡ አፍሬ፡ ይመልሱባታል፤

ወወላትው፡ ይበርቁ፤

ጋሻ፡ ለጋሻ፡ ይጣፋሉ፤ አንድም፡ የጠበራው፡ጋሻ፡ቦግ፡ቦግ፡ይላል፤

ወብዙኃን፡ አብድንት፡

ብዙ፡ ሬሳ፡ ይወድቃል፤

ወክቡድ፡ ድቀት፤

ጽኑ፡ መከራ፡ ይደረጋል፤

ወቀትል፤

ጽኑ፡ ሰልፍ፡ ይሆናል፤

ወአልቦ፡ ጽንዕ፡ ለሕዘቢሃ፤

ለሠራዊቶቿ፡ ጽንዕ፡ የላቸውም፤ አንድም፡ ጽኑዕ፡ ቢል፡ አርበኛ ውም፡ ጸንቶ፡ አይዋጋም፤

ወይደውዩ፡ በሥጋሆሙ፡ እምብዝኃ፡ ዝሙቶሙ፤

ከበደላቸው፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ በሥጋቸው፡ መከራ፡ ይቀበላሉ፤

፬፤ ዘማ፡ ሠናይት፡ ወፍሥሕት፡ ልሕቀቶሙ፡ ለሰብአ፡ ሥራይ፤

ያማረች፡ የተወደደች፡ ደስ፡ ያላት፡ ሥር፡ የሚምሱ፡ ሰዎች፡ [illegible] ነነዌ፤

እንተ፡ ትሠይጥ አሕዛበ፡ በዝሙታ፤

በጣዖቷ፡ ሠራዊቶቿን፡ የምትጐዳ፤

ወሕዝበ፡ በሥራያቲሃ፤

በሟርቷ፡ ሕዝቡን፡ የምትጐዳ፡ ነነዌ፤

፭፤ ናሁ፡ አነ፡ ላዕሌኪ፡ ይቤ፡ እግዚአ ብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እነሆ፡ በመዓት፡ አለሁብሽ፡ አለ፤

ወእቀፍፀኪ፡ እምድኅሬኪ፡ ውስተ፡ ገጽኪ፤

ፊት፡ ለፊት፡ ከወደኋላሽ፡ እገ ፍፍሻለሁ፤ ሴቶች፡ ከወደኋላቸው፡ ሲገፍፏቸው፡ ያፍራሉ፡ ኃፍ ረቷን፡ መናገር፡ ነው፤

ወአሬእዮሙ፡ ለአሕዛብ፡ ኃፍረተኪ፤

ኃፍረትሽን፡ ለሠራዊቶችሽ፡ እገ ልጽላቸዋለሁ፤

ወለነገሥት፡ ኃሣረኪ፤

ተዋርዶሽን፡ ለነገሥታቱ፡ እገ ልጽላቸዋለሁ፤

፮፤ ወእገድፍ፡ ላዕሌኪ፡ ርኵሰ፡ ዘከመ፡ ረኰስኪ፤

በጣዖት፡ የምትተዳደፊ፡ እንደ መሆንሽ፡ መከራ፡ አመጣብሻለሁ፤

ወእሰጥሃኪ፤

በመከራ፡ ሰጣ፡ አደርግሻለሁ፤ (እገልጥሻለሁ)

ወአረስሐኪ፤

የምታጸይፊ፡ አደርግሻለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእሬስየኪ፡ ኀስርተ።

የተዋረድሽ፡ አደርግሻለሁ፤

፮፤ ወኵሉ፡ ዘርእየኪ፡ ይዌርቅ፡ ላዕሌኪ።

ያየሽ፡ ሁሉ፡ በላይሽ፡ ላይ፡ ጢቅ፡ ይልብሻል፡ ማለት፡ ይጸየፍሻል፤

ወይብሉ፡ ጠፍዓት፡ ነነዌ፡ መኑ፡ ይግዕር፡ ላዕሌሃ።

ነነዌ፡ ጠፋች፡ ማን፡ ያዝንላታል፤

እምአይቴ፡ ተኃሥሥ፡ ዘይናዝዛ።

የሚያረጋጋት፡ ወዴት፡ ታገኛለች፤

፰፤ ወዘያስተዴሉ፡ መክፈልታ።

ገመድ፡ ጥሎ፡ ዕጣዋን፡ የሚካፈልላት፡ ማነው፤

ወዘይቀኒ፡ አውታሪሃ።

የበገናውን፡ ድንጉዙን፡ አማሪቱን፡ ለይቶ፡ የሚመታላት፡ ማነው፤ አንድም፡ አውራጃዋን፡ ሁሉ፡ የሚገዛ፡ ማነው፤

አንቲኒ፡ ትኄይሲ፡ እምነ፡ አሞን፡ እንተ፡ ትነብር፡ ማዕከለ፡ ባሕር።

በባሕር፡ መካከል፡ ከምትኖር፡ ከእስክንድርያ፡ ከጢሮስ፡ አንቺ፡ ትበልጫለሽ፤

ማይ፡ ሐፁራ፡ ወማይ፡ ጽንፉ፡ ወአረፋቲሃ።

አጥሯ፡ ቅጥሯ፡ ውሃ፡ ከሚሆን፡ ከእስክንድርያ፡ አንቺ፡ ትበልጫለሽ፡

፱፤ ወኢትዮጵያ፡ ኃይላ፡ ወግብፅ፡

ኢትዮጵያና፡ ግብፅ፡ ኖባ፡ ረዳቷ፡ ከሚሆኑ፡ ከእስክንድርያ፡ አንቺ፡ ትበልጫለሽ፤

ወአልቦ፡ ጽንፍ፡ ለምጕያያ።

የምትሸሽበት፡ የላትም፤

ወሊብያስ፡ ይረድዕዋ።

ኃያላኑ፡ ይረዱዋታል፡ ሊብያስ፡ አርማህ፡ እንዲል፤

፲፤ ወይእቲኒ፡ እምነ፡ ምንባሪሃ፡ ተዄወወት፡

ይችም፡ ነነዌ፡ ከሀገሯ፡ ተማርካ፡ ትሄዳለች፡

ወይወስድዋ።

ማርከው፡ ይወስዷታል፤

ወይነጽሕዎሙ፡ ለደቂቃ፡ ውስተ፡ ኵሉ፡ ፍናው።

ለሕፃናቲሃም፡ ይላል፡ ልጆቿን፡ በየጐዳናው፡ እየወጉ፡ ይጥሏቸዋል፤

ወይትዓፀው፡ ኵሉ፡ ክብራ።

ባለጸግነቷ፡ ሁሉ፡ ይማረካል፤

ወይሞቅሕዎሙ፡ ለመላእክቲሃ፡ ኵሎሙ።

አለቆቿን፡ ሁሉ፡ ያሥሯቸዋል፤

፲፩፤ ወአንቲኒ፡ ትሠክሪ።

አንችም፡ በመከራ፡ አረቂ፡ ትሠክሪያለሽ፤



ወትከውኒ፡ እብደ።

አእምሮሽን፡ ታጫለሽ፤

ወተኃሥሢ፡ ለኪ፡ ዘይባልሐኪ፡ እምፀርኪ።

ከጠላቶችሽ፡ የሚያድንሽ፡ ትፈልጊያለሽ፤

፲፪፤ ወኢያድኅኑኪ፡ አጽዋንኪ።

አምባዎችሽ፡ አያድኑሽም፤ አንድም፡ አርበኞችሽ፡ አያድኑሽም፤

ወይሜምዑ፡ መዓቅባንኪ።

ዘበኞችሽ፡ ይሸሻሉ፤

ወይወድቁ፡ ውስተ፡ አፈ፡ በላዒ።

በሰይፍ፡ አንደበት፡ ይወድቃሉ፤

፲፫፤ ናሁ፡ አሕዛብኪኒ፡ ከመ፡ አንስት፡ በውስቴትኪ።

እነሆ፡ በአንቺ፡ ውስጥ፡ ያሉ፡ ሠራዊቶችሽ፤ አንድም፡ አርበኞችሽ፡ እንደሴት፡ ይፈራሉ፤

ወይትረኃዉ፡ ለፀር፡ አናቅጸ፡ ብሔርኪ።

ያገርሽ፡ በሮች፡ ሁሉ፡ ለጠላቶችሽ፡ ይከፈታሉ፤

ወይበልዖሙ፡ እሳት፡ ለመናሥግትኪ።

ቁልፎችሽን፡ እሳት፡ ይበላቸዋል፡ ማለት፡ አርበኞችሽን፡ ጦር፡ ያጠፋቸዋል፤

፲፬፤ ናሁ፡ ማይ፡ አገተኪ።

እነሆ፡ ጦር፡ ከበበሽ፤

ፃዒ፡ ወአጽንዒ፡ አፅዋንኪ።

ይሆንልሽ፡ እንደሆነ፡ ወጥተሽ፡ አምባዎችሽን፡ አጽኚያቸው፤ አንድም፡ አርበኞችን፡ አጥኚያቸው፤

እርጊ፡ ምስለ፡ ጽቡር።

ከምክር፡ ጋራ፡ ውጪ፤

ወአፅብሪ፡ በኃሠር።

በጭድ፡ ለውሺው፡ ማለት፡ በምክር፡ አፅኚው፤

ወአይብሲዮ፡ በግንፋል።

ተኩሰሽ፡ ጡብ፡ አድርጊው፡ ማለት፡ በምክር፡ አጽኚው፤

፲፭፤ እስመ፡ በህየ፡ ትበልዓኪ፡ እሳት።

በዚያ፡ መቅሠፍት፡ ታጠፋሻለችና፤

ወታጠፍዓኪ፡ ኲናት።

ጦር፡ ታጠፋሻለች፤

ወይበልዓኪ፡ ከመ፡ አንበጣ።

አንበጣ፡ እንዲያጠፋ፡ ያጠፋሻል፤

ወትከብዲ፡ እምደጎብያ።

ኵብኩባ፡ መነሣት፡ እንዲሳነው፡ ለመማረክሽ፡ መመለስ፡ የለውም፤

፲፮፤ ወአብዛኀኪ፡ ተግባረኪ፡ እምኮከበ፡ ሰማይ።

በሰማይ፡ ካሉ፡ ከዋክብት፡ ይልቅ፡ ክፉ፡ ሥራሽን፡ አበዛሽ፤ አንድም፡ ጣዖት፡ ከማምለክሽ፡ የተነሣ፡ ለዌዋዌሽ፡ ሚጠት፡ የለውም፤

ደጎብያሂ፡ ነበረ፡ ወሠረረ።

ኵብኩባ፡ እስኪያድግ፡ ድረስ፡ እንዲቀመጥ ፡ከአደገ፡ በኋላ፡ ተነሥቶ፡ እንዲሄድ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፤ ወአምሠጡ፡ ድሙራንኪ፣

ትገዢያቸው፡ የነበሩ፡ እስራ ኤል፡ ሄዱ፤

ከመ፡ አንበጣ፡ ዘይነብር፡ ላዕለ፡ ጥቅም፡ በዕለተ፡ ጊሜ፡ ወቊር፣

በጉም፡ በብርድ፡ ቀን፡ አንበጣ፡ በቅጽር፡ ላይ፡ እንዲሰፍር፣

ወእምከመ፡ ሠረቀ፡ ፀሐይ፡ ይትገነሥ፡

ፀሐይ፡ በወጣ፡ ጊዜ፡ ተነሥቶ፡ እንዲሄድ፡ ትገዢያቸው፡ የነ በሩ፡ እስራኤል፡ ይሄዳሉ፤

ወኢያእመረት፡ ብሔራ፣

እሷ፡ ግን፡ አገሯን፡ አላወቀች ውም፡ ማለት፡ ለመማረኳ፡ መመ ለስ፡ የለውም፤

፲፰፤ አሉ፡ ሎሙ፡ እስመ፡ ደቀሱ፡ ኖሎትኪ፣

ነገሥታቱ፡ የሞት፡ እንቅልፍ፡ አንቀላፍተዋልና፡ ወዮላቸው፤

ንጉሠ፡ ፋርስ፡ አኖሞሙ፡ ለኃያላንኪ፣

አርበኞችሽን፡ ቂሮስ፡ የሞት፡ እን ቅልፍ፡ እንዲያንቀላፉ፡ አድር ጓቸዋልና፤

ወግዕዘ፡ አሕዛብኪ፡ ውስተ፡ አድባር፣

ሠራዊቶችሽ፡ ወደአምባው፡ ሸሹ፤

ወአልቦ፡ ዘይሬኢ

የሚያይሽ፡ የለም፤

ወአልቦ፡ ዘይጸንሕ፣

አንቺን፡ ደጅ፡ የሚጠናሽ፡ የለም፤

፲፱፤ ወአልቦ፡ ፈውስ፡ ለቊስልኪ፣

ለቁስለ፡ መከራሽ፡ድኅነት፡ የለውም፤

ኵሕሰ፡ ፀልዕኪ፣

ቁስለ፡ መከራሽ፡ ሰፋ፣ ይህንን፡ ናሆም፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ባንቺ፡ ጠፋልን፡ ሲል፡ ፊዋሲተ፡ ቍስሉ፡ ለናሆም፡ ብሎ፡ አባ፡ ሕርያ ቆስ፡ ወስዶታል፤

ወኵሎሙ፡ እለ፡ ሰምዑ፡ ዜናኪ፡ ይጠፍሑ፡ እደዊሆሙ፡ ላዕሌኪ፣

ያንቺን፡ ወሬ፡ የሚሰሙ፡ ሁሉ፡ እጃቸውን፡ ያጨበጭባሉ፤

እስመ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ በጽሐ፡ እከይኪ፡ በኵሉ፡ ጊዜ፣

ክፋትሽ፡ በየጊዜው፡ በሁሉ፡ ላይ፡ ደርሷልና፤

ተፈጸመ፡ ዘናሆም፡ ነቢይ፡ በረከተ፡ አምላኩ፡ የሃሉ፡ ምስሌነ፣ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፣

አነሣሥቶ፡ ለአስጀመረን፡ አስ ጀምሮ፡ ለአስፈጸመን፡ ለእግዚ አብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግ ባው፡ አሜን፡ በውነት።

# ዘዕንባቆም፡ ነቢይ

## መቅድም

ዕንባቆም፡ ማለት፡ ማእምር፣ ለባዊ፣ ነባቢ፡ ማለት፡ ነው፤ ይኸም፡ ዕንባቆም፡ አዝመራውን፡ ለሚያጭዱ፡ ምሳ፡ ይዞ፡ ሲሄድ፡ መልአኩ፡ ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ ሰድ፡ ዘንተ፡ ምሳሐ፡ ለዳንኤል፡ እትከ፡ ዘሀሎ፡ ውስተ፡ ግበ፡ ባቢሎን፡ አለው፣ ይኸንን፡ የያ ዝኸውን፡ ምሳ፡ በአናብስት፡ ጉድጓድ፡ ላለ፡ ለወንድምህ፡ ለዳ ንኤል፡ ውሰድለት፡ አለው፤ ዕን ባቆምም፡ ባቢሎንሃ፡ ኢየአምር፣ ባቢሎንን፡ አላውቃትም፤ ግበ፡ አናብስትሂ፡ ኢርኢኩ፣ የአናብ ስትንም፡ ጉድጓድ፡ አላየሁም፡ አለው፣ መልአኩ፡ በራሱ፡ ላይ፡ ተሸክሞ፡ ወስዶ፤ አንድም፡ በአ ንዲት፡ ጠጉሩ፡ አንጠልጥሎ፡ ወስዶ፡ በባቢሎን፡ ጣለው፣ የአ ንበሳው፡ ጉድጓድ፡ እንደተዘጋ፡ ገብቶ፡ ለዳንኤል፡ ምግቡን፡ ሰጥቶት፡ ሄዷል፤

ዳንኤልም፡ ተዘከረኒ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኢኃደጎሙ፡ ለእለ፡ ያፈቅርዎ፣

ትንኚን፡ በምግብ፡ የሚያስብ፡ እግዚአብሔር፡ አሰበኝ? ብሎ፡ አድንቋል፣ ይኸውም፡ ለጊ ዜው፡ ተደርጓል፡ ለኋላው፡ [illegible] በአናብስት፡ [illegible]

ግበ፡ ነፍስ፣ እንባቆም፡ የጌታ፡ ምሳሌ፡ ነው፤ እንደተዘጋ፡ ገብቶ፡ እንደተዘጋ፡ መውጣቱ፡ ጌታ፡ በኅቱም፡ ድንግልና፡ ተፀንሶ፡ በኅ ቱም፡ ድንግልና፡ ለመወለዱ፡ ምሳሌ፡ ነው፤ ዳግመኛ፡ አራቱ፡ ነገሥተ፡ ፍልስጥኤምን፡ ይዞ፡ አምስቱ፡ ነገሥተ፡ ምድያምን፡ ድል፡ ነስቷል፣ በዔዋዌም፡ ጊዜ፡ ፍልስጥኤም፡ ከምትባል፡ አምባ፡ ገብቶ፡ ድኗል፣ ትውልዱ፡ ነገዱ፡ ከነገደ፡ ስምዖን፡ ነው፣ አባቱ፡ ዳኮር፡ እናቱ፡ ሬፋ፡ ይባላሉ፣ መነሣቱ፡ በሕዝቅያስ፡ ዘመን፡ ነው፤

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ተረፈ፡ ዘርእየ፡ ዕንባቆም፡ ነቢይ፣

ናሆም፡ ከማየት፡ የቀረው፡ ዕን ባቆም፡ አይቶ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ አንድም፡ ጌታ፡ በእ ስራኤል፡ ከማናገር፡ የቀረው፡ ዕንባቆም፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤

፪፤ እስከ፡ ማዕዜኑ፡ እግዚኦ፡ ንኬ ልህ፡ ኀቤከ፡ ወኢትሰምዓነ፣

አቤቱ፡ እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ እንጮሃለን? አንተስ፡ ምነው፡ አትሰማን?

www.ethiopianorthodox.org